# ከኢትዮጵያዉያን ህብረት ለፍትህ በብርታኒያ (ኢህፍብ) የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ በሚመለከት የተሰጠ መግለጫ!

**30** ጁላይ 2016

የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይፈቅድ በመግደልና በማስፈራራት ስልጣን ላይ ተንጠልትሎ የሚገኘው ወያኔ የሰብአዊ መብት ረገጣዉን ወደ አስገና ከፍተኛ ደረጃ አሸጋግሮታል፡፡ የአማራ ክፍል በሆነው በወልቅይት በጠገዴና በጠለምት አካባቢዎች 25 አመት ሙሉ የአማራውን ዘር በማጥፍትና በማጽዳት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣ ሲካሄድ በአለም አቀፉ ማህበረሰብ ምንም አይነት የዉግዝትም ሆነ የማእቀብ እርምጃዎች አልተወሰደም፡፡

ወያኔ በኢትዮጵያዉያን አቅም ማጣትና በባእዳን እርዳታ ስልጣን ላይ ከተፈናጠጠ ጀምሮ ህዝቡን በዘር በመከፋፈልና ስለ ዲሞክራሲ ስለፍትህ ስለ ሰላምና ስለ ብሄር ብሄረሰብ የሚያስብ በመምሰልና በማጭበርበር በህዝባችን ላይ ከፍተኛ ግፍ በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡ ስርአቱ በአማራ በኦሮሞ በአኙዋክ በአፋር በሲዳማ በደቡብ ህዝቦችና ባጠቀላይ በኢትዮጵያውያን ላይ ዘግናኝ ወንጀሎችን ፈጽሞአል፡፡ በተለያዩ ቦታዎች ብዙ ሰዎች ከተወለዱበት አካቢያቸው መሬታቸዉን በመቀማትና በማፈናቀል ከነልጆቻቸው የትም ተበትነው እንዲቀሩ አድርጎአል፡፡

በሰሜን ጎንደር ወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመው ግፍ በብዙ መገናኛ ብዙሃን ስላልተዘገበ ነው እንጅ እጅግ አሳዛኝና የወያኔን የፍርሃት ጭካኔ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ በእብሪት የጎንደርን መሬት የትግሬ በማስመሰል ካርታ ሰርተዋል፡፡ መሬቱና ማንነቱ ከትግራይ በመጡ ህገወጥ ታ ጣቂዎች ተነጥቅአል፡፡ ሚስቶቹና ልጆቹ ተደፍረዋል፡፡ ነብስ ያወቁና ያላወቁ የአካባቢው ተወላጆች ታፍነው ተወስደዋል፡፡ የተማሩና ታሪክን የሚያዉቁ ሰዎች በተለያየ አሰቃቂ ሁኔታ (በጥይት በዱላ በመቀጥቀጥና በእሳት በማጋየት) ተገለዋል፡፡ ታማኝ የሆኑ የምርምር ሰነዶች 305 በግፍ የተገደሉ ሰዎችን ስም አንድ በአንድ ዘርዝረው በመዘገብ አስታዉቀዋል፡፡

ይሁንና የአካባቢው ህዝብ ህግና ስርአትን በማክበር "መሬታችን የጎንደር አካል ነው፡፡ እኛም አማሮች (ኢትዮጵያዉያን) ነን ስለዚህ በህገመንግስቱ መሰረት መብታችን ይጠበቅልን" በማለት ቢያመለክቱም ሰሚ አላገኙም፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ በህዝቡ የተወከሉትን የኮሚቴ አባላት በማስፈራራትና በማሳደድ ከትግራይ በመጡ ታጣቂዎች ህገወጥ አፈና ሲያካሂዱ ህዝቡ ራሱን በመከላከል በወያኔ አሸባሪና አፋኝ ቡድን ላይ ተመጣጣኝ ምት በማሳረፍ እራሱንና ማንነቱን ለማስከበር አምሮ መነሳቱን አሳይቶአቸዋል፡፡ ይህ ህዝባዊ እርምጃ ወያኔንና ጥቂት ለንዋይ የተገዙ ከሃዲ አገልጋዮቹን ከፍተኛ ፍርሃትና ጭንቀት ዉስጥ አስምጦአቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ወያኔ የፌደራል መንግስት እንዳለ ለማስመሰል ቢወሽክትም እዉነቱ ግን የፌደራል መንግስት እንደሌለ ከትግራይ የታጠቁ ሀይሎች ወደ አማራም ሆነ ወደ ሌሎች ክልሎች (የክልል አስተዳደር ተብዬዎች) በህገ ወጥ መንገድ እየገቡ ህዝቡን ማሸበራቸው ትልቅ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ አደገኛ ህግ አልባነት የአናሳዋን ወያኔን ዉርደትና ዉድቀት የሚያፋጥን እንጂ የሚጠቅማት አይሆንም፡፡

ሰሜን ጎንደር ዉስጥ በወልቃይት በጠገዴና በጠለምት አካባቢዎች የሚካሔዱ ትግሎች የቆዩና የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ጥቅምና ደህንነት መሰረት ያደረጉ ስለሆነ አማራው ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ስለዚህ ኢህፍብ  በጎንደርና በአካባቢው ህዝብ ላይ ወያኔ በመፈጸም ላይ የሚገኘዉን አፈናና ግድያ በጥብቅ ያወግዛል። ኢህፍብ የቀረበው ህጋዊ የማንነት ጥያቄ ተገቢ እንደሆነ በማመን ከህዝቡ ጎን መቆሙን እየገለጸ የመከላከያ ሰራዊቱም የያዘዉን መሳሪያ ልክ እንደ ኮሎነል ደመቀ ከህዝብ ጎን በመቆም አፈሙዙን ወደ ስርዓተ አልበኛው ወያኔ እንዲያዞር በዚህ አጋጣሚ አናሳስባለን።

ድል ለሰፊዉ የኢትዮጵያ ህዝብ!

ኢትዮጵያዉያን ህብረት ለፍትህ በብርታኒያ (ኢህፍብ)